# ድብቅ የሳንባ ነቀርሳ ኢንፌክሽን - ህክምና በማይሰጥበት ወቅት

የታካሚው መረጃ ከስዊድን ተላላፊ በሽታ ሐኪም

## ይህንን መረጃ ለምን አገኙሁት?

አንድ ምርመራ ድብቅ የሳንባ ነቀርሳ ኢንፌክሽን እንዳለቦት አሳይቷል።

እዚህ ምን ማሰብ እንዳለብዎት ይማራሉ።

## ድብቅ የሳንባ ነቀርሳ ኢንፌክሽን ምንድን ነው?

ድብቅ የሳንባ ነቀርሳ ኢንፌክሽን ማለት፥ በሳንባ ነቀርሳ ባክቴሪያ ተይዘዋል ማለት ነው፣ ነገር ግን በእሱ አልታመሙም ማለት ነው። አንድ ሰው በሳንባ ነቀርሳ ባክቴሪያ ሲጠቃ፥ የሰውነት በሽታ የመከላከል ስርዓቱ ምላሽ ይሰጣል፤ ይህም በደም ምርመራዎች ወይም በቆዳ ምርመራዎች ሊለካ ይችላል። በበሽታው የተያዙ አብዛኛዎቹ ሰዎች፥ ጤናማ ሆነው ይቀጥላሉ። ነገር ግን በኋለኛው ህይወታቸው፡ በሳንባ ነቀርሳ የመታመም አንነስተኛ አደጋ ሊያጋጥማቸው ይችላል።

## ድብቅ የሳንባ ነቀርሳ ኢንፌክሽን ያስተላልፋል?

አይ፣ ድብቅ የሳንባ ነቀርሳ ኢንፌክሽን ተላላፊ አይደለም። የቲዩበርክሎሲስ በሽታ የሚተላለፈው አንድ ሰው ሲታመም እና የሳንባ ነቀርሳ በሽታ በሳንባ ውስጥ ሲገባ ብቻ ነው።

## ለድብቅ የሳንባ ነቀርሳ ኢንፌክሽን ሕክምና አለ?

በሳንባ ነቀርሳ የመታመም ዕጣ ፈንታቸው ከፍ ያለ ሰዎች፥ በሽታ የመከላከያ መድኃኒት እንደሚሰጣቸው ይደረጋል። ይህ ለምሳሌ፣ ለህጻናት እና የተዳከሙ የበሽታ መከላከያ ስርዓቶች ላሏቸው ሰዎች ያገለግላል።

ሐኪምዎ ነው፡ አሁን ሕክምና **እንደማያስፈልግዎ** ገምግሞ የሚወስነው።

## ስለ ምን ማሰብ አለብኝ?

ምናልባት ወደፊት ረዘም ላለ ግዜ የሚቆይ (ሶስት ሳምንታት በላይ) የማሳል ሁኔታ፣ በሌሊት በላብ የመዘፈቅ ችግር፣ ትኩሳት ወይም ያልታለመደ የክብደት መቀነስ ካጋጠምዎት፥ የሳንባ ነቀርሳ ምርመራ እንዲደረግልዎት ሃኪምዎን መጠየቅ ይኖርብዎታል። ድብቅ የሳንባ ነቀርሳ ኢንፌክሽን እንዳለብዎት ይናገሩ።

እርጉዝ ከሆኑ ወይም በኢንሱሊን የሚታከም የስኳር በሽታ፣ ከባድ የኩላሊት በሽታ ካልዎት፣ የካንሰር ህክምና የሚያደርጉ ከሆነ ወይም በሌላ ምክንያት የተዳከመ የበሽታ መከላከያ ስርዓት ካጋጠምዎት፣ ድብቅ የሳንባ ነቀርሳ ኢንፌክሽን እንዳለብዎት፥ ለሐኪምዎ መንገር ይኖርብዎታል። ከዚያም በሳንባ ነቀርሳ ከመታመም ለመከላከል፥ የመከላከያ ህክምና ማድረግ ሊያስፈልግዎ ይችላል።

## የግንኙነት መረጃዎች (Kontaktuppgifter)

የታካሚዎች መቀበያ ክሊኒክ (Mottagning)…...…………………………………………...

…………………………………………………………………...……….…………

ስልክ ቁጥር (Telefon)…….……………………………………………………………